# እህ.ህ ወይ ነዶ!!!!

ከማተቤ መለሰ ተሰማ

አያበሳጭም ወይ እስኪ እየው ወገኔ፣
ተባለኮ አማራ ሽንታም በወያኔ፡
ይታይህ ያገር ልጅ ይህን የግፍ ስራ፣
ስው እንዲህ በዘሩ ሲሰደብ ሲአራ፡
እንዲህ ጉድ ይሰማል፡ እናንት ወይ ነዶ፣
ተሰደበ አማራ በቋንቋው ተዋርዶ፡
እርር ድብን ብሎ ተቃጠለ አንጀቴ፣
ስው እንዲህ በዘሩ ሲናቅ በማየቴ፡
ምነው አይቆረቁር አይገባ አጥንት ሰብሮ፣
ጀግናው ፈሪ ሲባል በባንዳ ደነቆሮ፡
ማንም የማይከደው ነበር ታሪክ ሰሪ፣
የሀገሩን ድንበር በህይወቱ አጣሪ፡
የሚዋረድበት እንዲህ በእየለቱ፣
ምንድን ይሆን ከቶ አማራ ጥፋቱ?
ለሀገሩ ክብር ከምር በታገለ፣
ዛሪ በከፋፋይ ሽንታም ነህ ተባለ፡
ከመንቋሸሽ በላይ ሰው እንዲህ በዘሩ፣
ምን መጥፎ ይመጣል እስኪ ተናገሩ፡
በቃ ተነስ እንጅ ምን ትጠብቃለህ፣
እንዴት በጠቅላላ ሽንታም ትባላለህ፡
ትግስትህ ከፍራት እንደዚህ ተቆጥሮ፣
ፈሪነህ ስትባል ተቀበልከው ድሮ?
ሞራልን የሚገድል የሚያስደፋ አንገት፣
ከዚህ የመረረ ምን ይምጣ ውርደት?
እንቢ በል!!! አማራ  አሁን በቃ ብለህ፣
እስከመቸ ድረስ ቆመህ ተሞታለህ?
በአንተ የደረሰው ነውና የሞት ሞት፣
ከእንግዴህ ተነሳ ይበቃል ዝም ማለት፡
ከእንግዴህ ተነሳ ይበቃል ዝም ማላት።

ኢሜልmatebemelese@yahoo.com